# ተማሪዎች፡- ምግብ ለመግዛት እርዳታ ይፈልጋሉ?
# በSNAP በኩል እርዳታ ሊያገኙ ይችላሉ!

**ተጨማሪ የምግብ እርዳታ ፕሮግራም (ሳፕሊመንታል ኑትሪሽን አሲስታንስ ፕሮግራም) (ስናፕ)**

- ✓ **SNAP ምንድን ነው?** SNAP በአብዛኞቹ የግሮሰሪ መደብሮች፣ ትላልቅ ሳጥን መደብሮች፣ ኮርነር መደብሮች፣ እና በአንዳንድ የኦንላይን ነጋዴዎች ሳይቀር ለመግዛት ሊጠቀሙበት በሚችሉት በኤሌክትሮኒክ በነፊት ትራንስፈር (ኢ.ቢ.ቲ.) ካርድ (እንደ ብድር ካርድ) በኩል ጥቅማጥቅሞችን የሚያቀርብ ፕሮግራም ነው።
- ✓ **የSNAP ጥቅማጥቅሞች ምን ያህል ናቸው?** ጥቅማጥቅሞች የሚወሰኑት አብረዋቸው በሚኖሯቸው ሰዎች ቁጥር (“ቤተሰብዎ”)፣ በገቢዎ፣ እና እንደ ቤት ኪራይ ያሉ አንዳንድ ወጪዎች ነው። ለቤተሰብዎ መጠን እስከ ከፍተኛው ጥቅማጥቅም መቀበል ይችላሉ።
- ✓ **ለSNAP ብቁ የሆነው ማን ነው?** ለSNAP የሚያመለክት እያንዳንዱ ሰው ከገቢው ገደብ በታች ገቢ ሊሆነው እና ሌሎች የብቃት መስፈርቶችን ማሟላት አለበት። ከግማሽ ሰአት በላይ በከፍተኛ ትምህርት ተቋም (እንደ ኮሌጅ፣ ዩኒቨርሲቲ፣ ወይም የንግድ ትምህርት ቤት) እየተማሩ ከሆነ፣ **ብቁ ለመሆን ከታች ከተዘረዘሩት መጠይቆች ውስጥ አንዱን ማሟላት አለብዎት።** እንዲሁም በኮቪድ-19 ወቅት ተጨማሪ መጠይቆች አሉ
- ✓ **ተጨማሪ መረጃ ማግኘት የምችለው እንዴት ነው?** በዲስትሪክቱ ስለ SNAP ተጨማሪ መረጃዎችን እዚህ ላይ ማግኘት ይችላሉ፡- https://dhs.dc.gov/snapinfo።

| ከፍተኛ የSNAP ጥቅማጥቅሞች<br>*ከኦክቶበር 1፣ 2022 - ሴፕቴምበር 30፣ 2023* | |
|---|---|
| **የቤተሰብ ብዛት** | **ከፍተኛ ወርሃዊ የSNAP ጥቅማጥቅሞች*** |
| 1 | $281 |
| 2 | $516 |
| 3 | $740 |
| 4 | $939 |
| *ከፍተኛው ጥቅማጥቅም በእያንዳንዱ ኦክቶበር 1 ይለወጣል | |

- **ማመልከት የምችለው እንዴት ነው?** ለማመልከት በርካታ አማራጮች አሉ። ሲያመለክቱ፣ ብቁነትዎን ለመወሰን ስለእርስዎ እና አብረዋቸው ስለሚኖሩት ሰዎች ጥያቄዎችን መመለስ አለብዎት። ማንነትዎን ለማረጋገጥ እንደ የመታወቂያዎ ግልባጭ ወይም ገቢዎን ለማረጋገጥ የደመዎዝ ክፍያዎች ሊያስፈልግዎት ይችላል።
  - ○ በኦንላይን በhttps://districtdirect.dc.gov/
  - ○ የዲስትሪክቱን የቀጥታ የሞባይል መተግበሪያ በመጠቀም (ለአይፎኖች እና ለአንድሮይዶች)
  - ○ በፋክስ፣ በፖስታ፣ ወይም በአካል ሊልኩት የሚችሉት የወረቀት ማመልከቻ (https://dhs.dc.gov/page/apply-recertify-benefits)
  - ○ በአገልግሎት ማዕከል ላይ በአካል። አንድ ለማግኘት፣ https://dhs.dc.gov/service/find-service-center-near-youን ይጎብኙ ወይም በ**(202) 727-5355** ወይም በነጻ የስልክ መስመር በ711 / (855) 532-5465 ይደውሉ።
- ✓ **ካመለከትኩ በኋላ ምን ይፈጠራል?** የSNAP ማመልከቻዎን አንዴ እንዳስገቡ፣ ብቁነትዎን ለመገምገም ለአጭር ቃለመጠይቅ ከዲስትሪክቱ ስልክ ይደወልልዎታል። እንደ ማንነትዎ እና ገቢዎ ያሉ የተወሰኑ ነገሮችን ማረጋገጫ እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ። ለSNAP ተቀባይነት ካገኙ፣ የኢ.ቢ.ቲ. ካርድዎን በፖስታ ይቀበላሉ፣ ከዚያም ምግብ ለመግዛት ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

**የኮሌጅ ተማሪ ብቁነት እና መጠይቆች**

ቢያንስ ለግማሽ ሰአት በኮሌጅ ወይም በሌላ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ውስጥ በመከታተል ላይ ከሆኑ፣ መደበኛ የብቁነት መስፈርቶችን ከማሟላት በተጨማሪ ለSNAP ብቁ ለመሆን **ከሚከተሉት መጠይቆች ውስጥ ቢያንስ አንዱን ማሟላት አለብዎት፡-**

- ➢ እድሜዎ ከ18 አመት በታች ወይም 50 አመት እና ከዚያ በላይ መሆን
- ➢ በፌደራል ወይም በስቴት ድጋፍ የሚደረግለት የስራ ጥናት ፕሮግራም ወይም በስራ ስልጠና ፕሮግራም ውስጥ መሳተፍ
- ➢ በሳምንት ቢያንስ ለ20 ሰአታት ለክፍያ የሚሰራ ከሆነ
- ➢ መስራት የማያስችል የአካል ወይም የአዕምሮ እክል ወይም የአዕምሮ ችግር መኖር
- ➢ ከ6 አመት በታች የሆነን ልጅ የሚንከባከቡ ከሆነ፤ ወይም የልጅ እንክብካቤ ማግኘት ካልተቻለ ከ6-11 እድሜ የሆነን ልጅ የሚንከባከቡ ከሆነ፤ ወይም ከ12 አመት በታች የሆነን ልጅ የሚንከባከብ የሙሉ ጊዜ ተማሪ ወላጅ ከሆኑ
- ➢ በተወሰነ የስራ ስልጠና ፕሮግራሞች በኩል በትምህርት ቤት ውስጥ የተመደቡ ከሆነ
- ➢ ለችግረኛ ቤተሰቦች ጊዜያዊ እርዳታ (TANF) የሚያገኙ ከሆነ

**<u>በኮቪድ-19 ወቅት ጊዜያዊ የተስፋፋ የተማሪ መጠየቂያ፡-</u>**


DC | DEPARTMENT of HUMAN SERVICES
WE ARE WASHINGTON GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
DC MURIEL BOWSER, MAYOR

# ተማሪዎች፦ ምግብ ለመግዛት እርዳታ ይፈልጋሉ? በSNAP በኩል እርዳታ ሊያገኙ ይችላሉ!

ለኮቪድ-19 የህዝብ ጤና ድንገተኛ በተሰጠው ምላሽ፣ ለአንዳንዱ የኮሌጅ ተማሪዎች የSNAP ብቁነት በህዝብ ጤና አስቸኳይ ጊዜ አዋጁ መጨረሻ ላይ ተስፋፍቷል። ከላይ ከተዘረዘሩት መጠይቆች በተጨማሪ ከእነዚህ መጠይቆች ውስጥ አንዱን ካሟሉ ለSNAP ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ፦

- በመደበኛ የትምህርት አመት ወቅት በስቴት ወይም በፌደራል በገንዘብ የሚደገፍ ስራ ጥናት ላይ ለመሳተፍብቁ ነዎት ነገር ግን እየተሳተፉ አይደለም። ለማረጋገጫ የሂሳብ እርዳታዎን ይጠይቁ።
- በዚህ የትምርት አመት $0 የሚጠበቅ የቤተሰብ አስተዋጽዖ (EFC) አለዎት። ተማሪዎች የፌደራል ማመልከቻ ለተማሪ እርዳታ (FAFSA)ን ካጠናቀቁ በኋላ EFC ይቀበላሉ። በፋይናንስ እርዳታ የሽልማት ደብዳቤዎ EFCን፣ የተማሪ እርዳታ ሪፖርትን ሊያገኙ ይችላሉ፣ ወይም የእርስዎን የተቋም የገንዘብ ድጋፍ ቢሮ መጠየቅ ይችላሉ።

***<u>በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች፦</u>***

**በSNAP ምን መግዛት ይችላሉ?**

እርስዎ በሚኖሩበት ቦታ ሊዘጋጁ የሚችሉ አብዛኞቹ ምግቦች በSNAP ጥቅማጥቅሞች ሊገዙ ይችላሉ፤ አልኮል፣ ትምባሆ፣ እና ትኩስ የተዘጋጁ ምግቦች በSNAP ሊገዙ አይችሉም።

**መጠይቁን ማሟላቴን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማሳየት አለብኝ?**

አዎ። ለምሳሌ፣ በስራ ጥናት ፕሮግራሞች ውስጥ እየተሳተፉ ከሆነ፣ እንደ የፋይናንስ ድጋፍ ሽልማት ደብዳቤ ያሉ ማስረጃዎችን ማሳየት ያስፈልግዎታል።

**ከወላጆቼ ጋር እየኖርኩ SNAP መቀበል እችላለሁ?**

ከ22 አመት በታች ከሆኑ እና ከወላጆችዎ ጋር የሚኖሩ ከሆነ፣ ለSNAP ማመልከት ይችላሉ፣ ነገር ግን ብቁነትዎን ለመወሰን የወላጆችዎ ገቢ እና ሌሎች መረጃዎች ከእርስዎ ጋር በአንድ ላይ ታሳቢ ይሆናሉ።

**የምግብ እቅድ እየተጠቀምኩ ከሆነ ለSNAP ብቁ ልሆን እችላእሁ?**

በዶርም ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ እና ከግማሽ በላይ ለሚሆን ምግብዎ የሚከፍል የምግብ እቅድ ካለዎት፣ ለSNAP ብቁ ሊሆኑ አይችሉም።

**በዲስትሪክቱ ውስጥ ለSNAP ብቁ ለመሆን በዲስትሪክቱ ውስጥ መሆር እና መማር አለብኝ?**

በኮሎምቢያ ዲስትሪክት (ዲስትሪክት) ውስጥ SNAP ለመቀበል፣ SNAPን እየተቀበሉ በዲስትሪክቱ ውስጥ መኖር አለብዎት፣ እና አድራሻዎን የሚያሳይ እንደ መታወቂያ ወይም የፍጆታ ክፍያ ያሉ ማስረጃዎችን ማሳየት አለብዎት። በዲስትሪክቱ ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ፣ ጥቅማጥቅሞችን ከሌላ ስቴት እየተቀበሉ ካልሆነ በስተቀር፣ በዲስትሪክቱ ውስጥ በሚኖሩበት ጊዜ ለSNAP ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ፣ በዲስትሪክቱ ውስጥ እየኖሩ በሌላ ስቴት ከተመዘገቡ እና ወደ ሌላ ትምህርት ቤት እየሄዱ ከሆነ እንደ ዲስትሪክቱ ነዋሪ ሊታሰቡ እና በዲስትሪክቱ ውስጥ የSNAP ጥቅማጥቅሞችን ሊቀበሉ ይችላሉ።

**የበለጠ ይወቁ**
https://dhs.dc.gov/service/snap-college-students

**ለSNAP ያመልክቱ**
https://dhs.dc.gov/page/apply-recertify-benefits



DC Department of Human Services
WE ARE WASHINGTON DC GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA MURIEL BOWSER, MAYOR